# የJKC ፖሊሲ - የሠራተኞች/መምህራን የአካል ቅጣት ወይም ኃይል አጠቃቀም / የተማሪ ሥነ-ምግባር/ሥነ-ስርዓት

የሚከተሉት መለኪያዎች/ስታንዳርዶች የት/ቤት ዲስትሪክት ሠራተኞች/መምህራን የተማሪን ሥነ-ስርዓት በሚያስጠብቁ ጊዜ ወይም ተማሪዎችን በሚቀጡበት ጊዜ የሚተገበሩ ይሆናሉ፡-

ሀ. አካላዊ ቅጣቶች፣ ለምሳሌ - ያጠፉ ተማሪን በኃይል መምታት/መግረፍ፣ መቀመጫ ላይ በእጅ መምታት፣ መቀመጫ ላይ በአርጩሜ መምታት ወይም መቆንጠጥ የተከለከለ ነው።

ለ. ለሚከተሉት ምክንያቶች ማንኛውም የት/ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ ተመጣጣኝ እና ተገቢ የሆነ የአካላዊ እርምጃ ወይም ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡-

1. ተማሪን ከአደገኛ ምግባረ ብልሹነት/ጥፋት ለማገድ፣

2. ማንኛውንም መሳሪያ ወይም አደገኛ ቁስ ለመንጠቅ፣

3. እራሱን/እራሷን ለመከላከል፣

4. ማንኛውንም ሰው ከጉዳት ለመጠበቅ፣ ወይም

5. ንብረትን ከውድመት ለመከላከል

ይህን ፖሊሲ ለማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት የት/ቤት ዲስትሪክት ባልደረባ እንደዚህ ማድረግ ያለበት ያለምንም የዘር፣ የፆታ፣ የብሔር፣ የኀሳ፣ የሃይማኖት፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም የፆታ ምርጫ ወይም የፆታ ማንነት መድሎ ይሆናል።

ይህ ፖሊሲ መተግበር የሚኖርበት በት/ቤት ዲስትሪክት ባልደረባ አባላት ሲሆን ትክክለኛ እና ሙያዊ ፍርድን በመጠቀም፣ ለት/ቤቱ ማኅበረሰብ አባላት ደህንነት፣ ሰላማዊነት እና ክብር ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ መሆን አለበት።

የጸደቀው፡- ጃኗሪ 15 ቀን 2009